# <u>አድዋና እኛ</u>

በልጅግ ዓሊ

የአድዋ በዓል አለፈ። ዓመት ጠብቀን እንደገና እናከብረዋለን። ድሮ ድሮ አድዋ ሲባል . . . የድል ቀን . . . የጥቁሮች ድል . . . አውሮፓውያን የተሸነፉበት . . . ጀግኖች . . . ምኒልክ . . . ጣይቱ . . . አሉላ አባነጋ . . . ገበየሁ . . . ባልቻ አባነፍሶ . . ሌሎችም አባበሎችና ስሞችን እንሰማ ነበር። የአደዋ በዓል እንደ ድሮ አይደለም። ተቀይሯል። ዛሬ ደፍሮ፡ -

ምንሊክ ተወልዶ ባያነሳ ጋሻ፣
ግብሩ እንቁላል ነበር ይሄን ጊዜ አበሻ . . .

ብሎ የሚገጥምም አይገኝም። ዘንድሮ ግብራችን እንቁላል እንዳይሆን ምኒሊክ ከለከሉን የሚልና የሚከስ ዘመናዊ አይጠፋም። አሁን አሁን ሁሉን ነገር ከዘር ፖለቲካ አንጻር መመልከት ተጀመረና የአድዋ በዓልም ከዘመኑ ጋር ተለወጠ። ከምኒልክ የአድዋ ጀግንነት በላይ ጥፋታቸው አጉልተው የሚያሳዩ ደልቃቃዎች ተፈጠሩ። ያ ለጥቁሮች ሁሉ ድል የተባለው አድዋን የመሩት ምኒልክን መስደብ እንደ ፋሽን ታየ፤ እንደ ዘመናዊ ፖለቲከኛነት ተቆጠረ።

ገበየሁ ቢሞት ተተካ ባልቻ፣
መድፍ አገላባጭ ብቻ ለብቻ ።

የተባለው የጀግና ሙገሳ ቀረ። <<ባልቻ አባ ነፍሶ ኦሮሞነት የማይሰማቸው ስለሆኑ ኦሮሞ አይደሉም>> የሚል የጠባብ ፖለቲከኞች ትንተና ተጀመረ። እንኳን እሳቸው ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት አሁን በቁም ያሉት አቶ ቡልቻ ደመቅሳ ኢትዮጵያዊነትን ስለሚቀበሉ ኦሮሞ አይደሉም ተብለው ሲወነጀሉ ሰምተን ምን አልን? ምንም። ስም ማጥፋት ለአንዳንዶች የተፈቀደላቸው <<የዴሞክራሲ>> መብታቸው ነው። ማንም የሚናገራቸው የለም። አንዱ ጎበዝ ከተናገረም በኢሳያስ አፈወርቂ ሰርጎ ገብ ጦር በስድብ ያስደበድቡታል።

ምኒልክን መስደብ የአዋቂነት መለኪያ፣ የዴሞክራትነት ጣራው የሚመስለቸው ብዙ ናቸው። ስለ አድዋ ትልቅነት ከተናገርክ ወይም ከጻፍክ አንተን አያድርገኝ። ሌላው ቢቀር ነፍጠኛ . . . ትምክተኛ . . . ቅኝ ገዢ. . . ባርያ ፈንጋይ ትባላለህ። እስቲ ደፍረህ ስለ ምኒልክ ጀግንነት አውራ፤ መብረቅ ይሁን ኤሌክትሪክ የያዝከው አታውቀውም፤ በስድብ ሞገድ ያነዝሩሃል። ፊት ለፊት ባይሰድቡህም በአሽሙር አይምሩህም። ስድብ ምን ቢያጡ አርጅተሃል ማለታቸው አይቀርም። መቸም የዚያን ሰሞን እንዳንተ አያውለኝ። ባሻ አውአሎም ሀረጎት የአድዋ ጦርነት ላይ ለጣሊያኑ ጀኔራል ባራቴሪ ምን እንዳሉት ታውቃለህ? <<እስሀ ዝዋአልካዩ አያውለና>> አሉት። ውሎህን አያውለኝ ማለታቸው ነው።

ለምን እንዳሉት ላጫውትህ? በአድዋ ጦርነት ወቅት ጦሩን እየመገቡ ማቆየት ለነ ምኒልክ አስቸጋሪ ሆኖ ነበር። በአስቸኳይ ጦርነቱ ካልተጀመረ በምኒልክ በኩል ችግር ሊፈጠር ሆነ። ጣሊያን ያለበት ሄደው እንዳይወጉት ቦታው አመች አልነበረም። ተመካከሩ። ወሰኑ ። ባሻ አውአሎም ሀረጎት ተጠርተው ተነገራቸው። ጀግናው ተስማሙ። ወደ ጣሊያን ሠፈር ሄዱ። ንገሩ የተባሉትን በኢትዮጵያ በኩል ስንቅ ማለቁንና በሽታ መግባቱን ለጄነራል ባራቴሪ ነገሩት። ተደሰተ። የካቲት 23 አደዋ ደረሰ። ባሻ አውአሎም ሀረጎት የአሉላ አባነጋን ጦር ሲመለከቱ ሮጠው ወደ እነ አሉላ ምሽግ ውስጥ ገቡ። ባራቴሪ . . . <<አውአሎም . . አውአሎም>> ብሎ ሲጠራቸው <<እስሀ ዝዋአልካዩ አያውለና>> አሉት ይባል።

አንተም ተሳስተህ ስለነ አሉላ ጀግንነት ከተናገርክ አንተን አያድርገኝ። የምኒልክ ጠላት ተጠራርቶ ጦሩን ይሰበቅብሃል። ሌላው ቢቀር እድሜህ ተቆጥሮ ማርጀትህ ይነገርሃል . . . ምን ማርጀትህ ብቻ፣ ሕልውናህም ተክዶ <<አለ እንዴ?>> ተብለህ ትጠየቃለህ ? ይህ ቀልድ እንዳይመስልህ። አንድ ጊዜ አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስን ተከላክዬ እነ አይነኬን ነክቼ፣ ከእኔ አልፎ ስንቱ ተሰደበ መሰለህ?

የምኒልክ ሃጢያት ከባርያ ፈንጋይነት እስከ ቅኝ ግዛት አስፋፊነት . . . ከነጭ እስከ ጥቁርነት . . . ከፈረንጅ አጎብዳጅነት እስከ ተገዥነት በየዘርፉ ይነገርሃል። እያንዳንዱ የግሉን ዓላማ ለማስፈጸም ከጠቀመው ምኒልክን ወቅሶ ይጽፋል።

ለምሳሌ ኤፍሬም ማዴቦ <<Negotiation, nation building, and the naysayers>> በሚል ርዕስ በድረ ገጽ ለንባብ ባበቃው ጽሁፉ ምኒልክን ከመለስ አመሳስሎ ነው ያስቀመጠቀው።

የግንቦት ሰባት ድርጅት መሪ የሆነው ኤፍሬም ማዴቦ <<መለስም ይሁን ምኒልክ ኢትዮጵያን ከፋፍለዋታል>> ባይ ነው። ምኒልክን ከመለስ ጋር ማወዳዳር ያስፈለገበት ጉዳይ ድርጅቱ ሰሞኑን ለሚያራምደው ፖለቲካ የሚያመቸው መንገድ ይህ ብቻ ስለሆነ ነው። ይህ አባባሉ በታሪክ አዋቂዎች መንደር ያስደንቀዋል ብዬ አላምንም። ምንአልባት ጥሩ ጭብጨባ የሚያስገኝለት በደጋፊዎቹ ስብስባ ላይ ከተነገረ ብቻ ነው።

መቼም ለብዙ ኢትዮጵያውያን የመለስና የምኒልክ ልዩነት ግልጽ ስለሆነ ለመተንተን ጥረት አላደርግም። ምን ታሪክን ብናጣምም ሁለቱ አንድ ሊሆኑ አይችሉም። ካለፈው <<ጥፋት>> በመማር ወደፊት የተሻለ ለመሥራት መዘጋጀት ባልከፋ። ታሪክን አጣሞ ለወቅታዊ ሁኔታ በሚስማማ መንገድ ማቅረብ ደግሞ የሚያሳፍር ነው። አቶ ኤፍሬም ለኢትዮጵያ አንድነት እታገላለሁ ካለ ለየትኛዋ ኢትዮጵያ እንደሆነ የሚታገለው ማስረዳት አለበት። ለምኒልክ ወይስ ገና አዲስ ለምትፈጠረው?

ኤፍሬም ማዴቦ ምንሊክን በቅኝ ገዥነት ሲከስ ፋሽሽቱ መንግሥቱ በጻፈው ድሪቶ ገጽ 47 ላይ <<ምኒሊክ ባርነትን አስፋፉ>> የሚል ሰፍሯል። መንግሥቱ ይህንን ካለ የሚገርም ነው። ይህ አቋም የመንግስቱ ይሁን የመጽሐፉ አራሚዎች የሚያጠያይቅ ነው። መንግሥቱም ሆነ ብዙ የተነገረላቸው የመጽሐፉ አራሚዎች በአዲሱ የዘር ፖለቲካ እየደነሱ እንደሆነ ነው የሚያሳየው እንጂ እውነትነቱ የጎላ አይደለም። የመንግስቱና የአራሚዎቹ ትግል ደግሞ ሌላ ነው። የመንግሥቱን ታላቅነት ለማውራት ቀደምት መሪዎችን ጥላሸት መቀባት የሚል ሆኖ እናገኘዋለን። ውለን አድረን ደግሞ የመንግሥቱን ፍርጠጣ ጀግንነት ለማድረግ አፄ ቴዎድሮስ ራሳቸውን የገደሉት <<ፈሪ>> ስለሆኑ ነው የሚል ብናነብ መደነቅ የለብንም።

ምኒልክ ላይ የሚደረገው ስም ማጥፋት በዚህ ብቻ አላበቃም። የምኒልክ ታሪክ የመንገደኛ ቦዘኔ ደራሲ የአግድሞሽ የዝሙት ልብ ወለድ ሆኖ ነው የከረመው። እንዲያውም ሰሞኑን ከምኒልክ ወደ ቴዎድሮስም ተሸጋግሮ ድረ ገጾችን አጣቦ ነበር። ደራሲው በእውኑ ዓለም ከመለስ ወደ ኢሳያስ አልጋ ጠባቂነት እንደተላለፈው በልብ ወለድ ጽሁፉም የቴዎድሮስና የምንልክ አልጋ አንጣፊ ሆኖ ሰንብቷል።

ድረ ገጾች ደግሞ ያንን እየተቀበሉ አስፋፍተውታል። ለሰሞኑ መደበሪያ ያህል አዲስ ሃሜት ካገኘን ምን ቸገረን? የጀግኖች ታሪክ በቅጥረኛ ደራሲያን ሲወላገድ በየድረ ገጹ እየለጠፍን ለመጪው ትውልድ የውሸት ታሪክ ማስተላለፍ ነው። ድረ ገጾችን አንባቢ አግኝቶ በተመልካች ቁጥር ውድድር አንደኛ ይሁን እንጂ! ሰሞኑን ለፈጠርነው ሕብረት ሙጫ ሁኖ ያፋቅረን እንጂ! ፈሪነታችንን እንደ ጀግንነት ያስቆጥርልን እንጂ! ምኒልክ ተሰደቡ አልተሰደቡ ምን አዲስ ነገር ሊመጣ።

ምኒልክ የሉም። ታሪካቸውን መከላከል አይችሉም። ለታሪክ ተቆርቁሮ አይሆንም ብሎ የተከራከረ ካለ ደግሞ ይሰደባል፣ ይዋረዳል። የሃገሪቷ ታሪክ አዋቂዎች የዘመኑ ፖለቲከኞች. . . አርጅታችኋል . . . ኋላ ቀር አስተሳሰብ . . . አሮጌ ፖለቲካ. . . የሚለውን አዋራጅ ስድብ ሽሽት ወይም በወያኔ የዘር ፖለቲካ ዋዠቀው ይህንን ደባ ለመዋጋት ብዕራቸውን እንኳን ማንሳት ተስኗቸዋል። ምንድነው ለሚቀጥለው ትውልድ የምናስተላልፈው? ይህንን የፈጠራ የውሸት እንቶ ፈንቶ? ይህንን የገንጣይና የተገንጣይ የስም ማጥፋት ዘመቻ? ጎበዝ ከሚጠፋው ስማችን፣ ከሚሰደበው ስብዕናችና ከፖለቲካው ክፍፍል ባሻገር ሃገራችንን እንውደድ! ከግል የሥልጣን ጥማችን ባሻገር የሃገራችንን ታሪክ እንጠብቅ። ያቺ ሃገር የተመሰረተችው እኮ እንደ አድዋ ባለው ሁሉም የሃገሪቱ ዜጎች በወደቁበት የጀግንነት ታሪክ ላይ ነው።

በድሉ ዋቅጅራ የተባለ ደራሲ ልጁን ኬር ዓለም ስለ ሃገሩ ያስተማረው እንዲህ ብሎ ነበር።

የኔ ልጅ

አያት ቅም አያትሽ፣ሰላም ሲሆን ከወልቂጤ አድማስ ማዶ ሽቅጦ
ሲያቀና ወረቱን ፣
ለእኔና ለአንቺ መኖሪያ ሲያቀና ቀዬና ቤቱን፣
ሀገር ጠላት ሲደፍራት ጦሩን ሰብቆ እየፎከረ፣
ከኦሮሞው ከትግሬው ከአፋሩ ከወላይታው ከሁሉም የጦቢያ ልጆች ፣
አጥንቱን እየማገረ፣
ሀገር ይሉት መግባቢያ ፣ሰንደቅ ይሉት መለያ ፣ሲያቆይልሽ
በጉራግኛ የማትገልጭው በጎጥ የማትገድቢው፣ ስንት አለ ታሪክ መስለሽ።
ለዚህ ነው ሀገር ይሉት ቋንቋ ላንቺ የሚያስፈልግሽ
ከወልቂጤ አድማስ ማዶ፤ ለተሳሰረ ታሪክሽ
ከወልቂጤ አድማስ ማዶ፣ለተወጠነው እድገትሽ።

እና ልብ በይ ልጄ ! ሀገር ማለት ቋንቋ ነው ባንደበት አይናገሩት ፣
በጆሮ አያዳምጡት።

ዛሬ በሃገራችን የጀግኖቻችን ስም እየጎደፈ ነው። አዲስ  በዘር ላይ የተመሠረተ ታሪክም ለመጻፍ የሚደረገው ጥረት ብዙ ነው። ይህ ታሪክ የማጥፋቱ ዘመቻ ከወያኔ አልፎ ሻዕብያዎችና አፍቃሬ ሻዕብያዎች በሰፊው ተያይዘውታል።

የትውልድ የጀግንነት ተግባር ቀጣይነት የማይፈልጉ በተለይ በአሁኑ ወቅት ጀግኖችን እያዋረዱ በመጻፍ ላይ ናቸው። የጀግኖቻችንን ታሪክ በተራ የዝሙት ታሪክ በመበረዝ፣ ቀጣዩ ትውልድ በጀግኖቻችን ታሪክ እንዳይኮራ፣ ሞራሉ እንዲላሽቅ እያደረጉ ነው። እነዚህ የእባብ ስብስቦች የሚረጩት መርዝ ምን ያህል አጥፊ እንደሆነ ያውቁታል። ትንሽ አዋራጅ ሃሜት ከብዙ የጀግንነት ታሪክ የበለጠ የመስፋፋት ኃይል እንዳላት ይረዱታል።

ጀግኖቻችን ታሪክ መጠበቅ የሚያስፈልግበት ጉልህ ምክንያት የጀግና ታሪክ ጀግናን ይፈጥራልና ነው። ቀጣዩ ትውልድ ባለፈው ታሪኩ እየኮራ ሃገሩን ይጠብቃል። የሚተካው ትውልድ በእነዚህ ጀግኖች ታሪክ እየተማረ አዲስ ጀግነንነትን ይሠራል። የኢትዮጵያ ጠላቶች ሊበርዙት የሚፈልጉትን የጀግኖቻችንን ታሪክ መከላከል የሁላችንም ተግባር መሆን አለበት።

አንድ ወቅት ሎሬት ጸጋዬ አንድ ስብሰባ ላይ የተጠየቁት ጥያቄ ትዝ ይለኛል። <<ስለ አፄ ቴዎድሮስ ሁል ጊዜ እያሞገሱ ለምን ይጽፋሉ?>> ተብለው ሲጠየቁ <<አይ ሌላውንማ የኢትዮጵያ ጠላቶች ይጽፉታል>> ነበር ያሉት።  ስሞኑን ሎሬት የተነበዩትን በገሃዱ ሕይወታችን እያነበብን ይሆን?

ሰለ ጀግኖቻችን የሚያስቡ ሁሉ በሰላም ይከረሙ !

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኖራለች!
ሎን ዶን የ ካ ቲ ት 2004

Beljig.ali@gmail.com